የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 26
ADDIS ABABA 11th February 2013

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፹፩/፳፻፭

ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት እና ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.........ገፅ ፷፰፻፫

CONTENTS

Regulation No. 281/2013

National Planning Council and National Planning Commission Establishment Council of Ministers Regulation ........................................................ Page 6803

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፩/፳፻፭ ዓ.ም.

## ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤትን እና ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት እና ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፩/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባን እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 281/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL PLANNING COUNCIL AND THE NATIONAL PLANNING COMMISSION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

### PART ONE

### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "National Planning Council and the National Planning Commission Establishment Council of Ministers Regulation No. 281/2013".

**2. Definition**

In this Regulation "Regional State" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations.

## ክፍል ሁለት

## ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት

**፫. መቋቋም**

ብሔራዊ የፕላን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**፬. የምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትር..............................ሰብሳቢ፣

፪/ የካቢኔ ሚኒስትሮች ..........................አባላት፣

፫/ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች ..................አባላት፣

፬/ የክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች.........አባላት፣

፭/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ..............አባል፣

፮/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች አካላት .................................. አባላት፡፡

**፭. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የአሥራ አምስት ዓመት የረጅም ጊዜና የተከታታይ አምስት ዓመታት አጠቃላይ የአገራዊ የምርት እና አጠቃላይ የአገራዊ ምርት የነፍስ ወከፍ ድርሻ እድገት ግቦችን ይጥላል፣

፪/ በየአምስት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የፕላን አዘገጃጀትና የልማት የቅድሚያ ትኩረት አቅጣጫዎችን በሚመለከት መመሪያ ይሰጣል፣ በመጨረሻም የተዘጋጀውን ፕላን ያጸድቃል፣

፫/ በብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን በየጊዜው በሚቀርብለት የፕላን አፈጻጸም ግምገማ ውጤት ላይ ይመክራል፣ ፕላኑ በፌደራልና በክልል አስፈጻሚ አካላት ተቀናጅቶ መተግበሩን ያረጋግጣል፡፡

**፮. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ የምክር ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## PART TWO

## THE NATIONAL PLANNING COUNCIL

**3. Establishment**

The National Planning Council (hereinafter the "Council") is hereby established.

**4. Members of the Council**

The Council shall have the following members:

1/ The Prime Minister.........................Chairperson;

2/ Cabinet Ministers ........................... Members;

3/ Chief Executives of Regional States......Members;

4/ Deputy Chief Executives of Regional States........................................ Members;

5/ Governor of the National Bank of Ethiopia........................................ Member;

6/ Other organs to be designated by the Prime Minister........................................Members.

**5. Powers and Duties of the Council**

The Council shall have the powers and duties to:

1/ set overall targets of growth of gross domestic products and gross domestic products per capita for the long term period of fifteen years and the breakdown of successive five-year periods therein;

2/ provide guidance for planning and development priorities at the commencement of each five-year plan and finally approve the plan;

3/ review the periodic evaluation results of the plan submitted by the National Planning Commission and ensure its integrated implementation by federal and regional executive organs.

**6. Meetings of the Council**

1/ The Council shall hold its regular meetings once every year; provided, however that it may hold extraordinary meetings at any time where necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Council are present at a meeting.

3/ The Council shall pass its decisions by majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

## ክፍል ሦስት

## ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን

**፯. መቋቋም**

፩/ ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) በህግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

**፰. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።

**፱. ዓላማ**

የኮሚሽኑ ዓላማ በተመጣጠነ አገር አቀፍ የዕድገት ማዕቀፍና በአሥራ አምስት ዓመታት የረጅም ጊዜ አመላካች ፕላን ላይ በመመሥረት የየአምስት ዓመት አገራዊ የልማት ፕላን ማዘጋጀትና አፈጻጸሙን በየጊዜው መገምገም ይሆናል።

**፲. ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፣ እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ ይሰጣል፤

፪/ በፕላኑ የተቀመጠውን ዓመታዊ አጠቃላይ አገራዊ የምርት ዕድገትን ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት እድገት መነሻዎችን ይገምታል፤

፫/ ከአጠቃላይ አገራዊ የምርት እድገት ግቦችና ከፖሊሲና ከህግ ሪፎርም እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት እና የወጪና የገቢ ንግድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤

፬/ ከአጠቃላይ አገራዊ ምርት የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎችን የተናጠል ድርሻ ይለያል፤

፭/ ፕላኑ ትግበራውን ለመምራት እንዲያስችል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከቱትን የኢኮኖሚ ዘርፎች ከንዑስ ዘርፎቻቸው እስከ ምርት ዓይነቶቻቸው ወይም የኢንዱስትሪ ክፍሎቻቸው ድረስ ይተነትናል፤

፮/ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ግብዓቶችን አቅርቦት ለመተመን በግብርናና በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል፤

## PART THREE

## THE NATIONAL PLANNING COMMISSION

**7. Establishment**

1/ The National Planning Commission (hereinafter the "Commission") is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The Commission shall be accountable to the Prime Minister.

**8. Head Office**

The Commission shall have its head office in Addis Ababa.

**9. Objective**

The objective of the Commission shall be to prepare five-year plans of national development in the framework of country wide balanced growth within the context of a long term perspective plan of fifteen years, and conduct periodic evaluation of the implementation of the plans.

**10. Powers and Duties of the Commission**

The Commission shall have the powers and duties to:

1/ serve as secretariat of the Council and provide support as needed;

2/ conduct assessment of growth factors in terms of increase in capital and productivity necessary for the attainment of the annual growth in gross domestic products set in the plan;

3/ formulate macro-economic targets of savings, investment, exports and imports which are consistent with the growth target of gross domestic products, and reform measures pertaining to policies and legislations;

4/ set the breakdown of gross domestic products into its component sectors of agriculture, industry and services;

5/ disaggregate the sectors referred to in sub-article (4) of this Article into their sub-sectors, and further down to groups of products or branches of industry to enable the plan to guide the implementation;

6/ analyze the inter-industry demand for the agricultural and manufacturing sectors so as to particularly assess availability of inputs both from domestic sources and through imports;

፯/ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚ ተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎችን የሚዘረዝር የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፤

፰/ የፌደራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና የክልል ቢሮዎች አንድን የዘርፍ አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በየበኩላቸው የሚፈጽሟቸውን ተግባራት የሚያ ሳይ የተቀናጀ የፕላን አፈጻጸም መርሐ ግብር ያዘጋጃል፤

፱/ የፕላን አፈጻጸሙን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

፲/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ፲፩. የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾሙ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር፤ እና

፪/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

## ፲፪. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራ ይመራል፣ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኮሚሽኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ኮሚሽኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደር ጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ) የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል።

7/ draw out sector plans iteratively in consultation with the relevant federal and regional executive organs, detailing programs and projects to be undertaken as well as reform measures pertaining to policies and legislations;

8/ formulate plan implementation matrix by line ministries at the federal level and regional bureaus showing actions to be undertaken covering the entire sector plan;

9/ conduct periodic monitoring and evaluation of the plan implementation;

10/ perform other activities necessary for the attainment of its objective.

## 11. Organization of the Commission

The Commission shall have:

1/ a Commissioner and Deputy Commissioner to be appointed by the government; and

2/ the necessary staff.

## 12. Powers and Duties of the Commissioner

1/ The Commissioner shall be the chief executive officer of the Commission and shall direct and administer the activities of the Commission.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Commissioner shall:

a) exercise the powers and duties of the Commission stated under Article 10 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Commission in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare the work programs and budgets of the Commission and implement same upon approval by the government;

d) effect payments in accordance with the approved work program and budget of the Commission;

e) represent the Commission in all its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Office of the Prime Minister the performance and financial reports of the Commission.

፫/ ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ኮሚሽነሩ እና ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፲፫. <u>በጀት</u>

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

## ፲፬. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ፲፭. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ The Commissioner may delegate part of his powers and duties to the Deputy Commissioner and other officers and employees of the Commission to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Commission.

## 13. <u>Budget</u>

The Commission's budget shall be allocated by the government.

## 14. <u>Books of Accounts</u>

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

## 15. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 11th day of February, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**